
## ሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች ለማድረግ ቃል የሚገባቸው

በሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አስተማማኝ እና እንግዳ ተቀባይ የሆኑ አካባቢዎች ለመፍጠር በቁርጠኝነት ስንሠራ፣በሁሉም የትምህርት ቤቶቻችን የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ያለውን የዘር አለመመጣጠን አውቀን ሁሉም ተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን እና ግንኙነቶችን ለመፍጠር በትጋት እንሰራለን።ተማሪዎች እንደ እውነተኛ ማንነታቸው መታየት ሲችሉ፣በትምህርት ቤት ውስጥ ትልቅ ግምት፣አቀባበል እና ደህንነት ይሰማቸዋል፣እና የመሳተፍ፣ ትምህርት ቤት የመቆየት እና የመማር እድላቸው ሰፊ ይሆናል።

ይህንን ለማሳካት፣የሚከተሉትን ማድረግ ያስፈልገናል:

- ተማሪዎች በአካዳሚክ፣በስነምግባር፣በማህበራዊ እና ስሜታዊ ለመደገፍ በመረጃ የተደገፈ እና ባህላዊ ምላሽ ሰጪ ልማዶችን በመጠቀም ተማሪዎች እንዳይማሩ የሚያደርጋቸውን መሰናክሎች ማስወገድ፤
- አካታች ያልሆኑ ልምዶችን ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ በተማሪ ተሳትፎ እና የምረቃ መጠን ላይ የሚያስከትለውን የማይካድ ጉዳት እና ተፅእኖ መፍታት፤የተማሪን መነሳሳት፣መማር እና የባለቤትነት ስሜትን ማዕከል ያደረጉ አካታች እና እንግዳ ተቀባይ አካባቢዎችን ማቅረብ ፤
- ተማሪዎች እንዲማሩ እና የሚያውቁትን እንዲያካፍሉ ተለዋዋጭ አማራጮችን የሚሰጥ ትምህርትን መንደፍ፤
- የበለጠ አካታች እና ፍትሃዊ ትምህርት የሚያረጋግጡ አማራጮችን ለመፍጠር የተማሪ ድምጽ መጠቀም




## የትምህርት ቤት እና የሰራተኞች ሀላፊነቶች:

የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ሰራተኞች የሚከተሉት ሓላፊነቶች ኣሏቸው:

- ተማሪዎች የታዩ፣የተሰሙ እና የተከበሩ እንዲሰማቸው የሚያደርግ አካታች፣ደህንነቱ የተጠበቀ እና እንግዳ ተቀባይ የሆነ አካባቢ ማረጋገጥ፤
- ተማሪዎችን ማወቅ፣አዎንታዊ ግኑኝነት መፍጠርና መንከባከብ
- የተማሪን የስነምግባር ጉድለት ለመፍታት የቃል መከላለያ ችሎታን መጠቀም፤
- ተማሪዎች ከስህተቶች እንዲማሩ ባህላዊ ምላሽ ሰጪ፣ማህበራዊ እና ስሜታዊ ድጋፍ መስጠት፤
- የትምህርት ጊዜን ከፍ በማድረግ የተማሪ እና ት/ቤት ግንኙነት በትንሹ የሚረብሹ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን መተግበር፣
- ፍላጎቶቻቸውን ለመለየት እና ለመርዳት ከተማሪዎች እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር መተባበር፤ከባህል ምላሽ ሰጪ እና ጉዳት ከደረሰበት መነፅር እየሰሩ፣የራሳቸውን ስውር አድሎአዊነት መመርመር፤
- የፀረ-ዘረኝነት ተግባራትን የሚያበረታቱ ሙያዊ ትምህርት መፈለግ፣ መሳተፍ እና መከታተል።

## የትምህርት ቤት ደህንነት እና ጥበቃ አገልግሎቶች ፕሮግራም

የደህንነት እና የጥበቃ ሰራተኞች የትምህርት ቤቱን ደህንነት ለመጠበቅ የእያንዳንዱን ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር ይደግፋሉ።እንደ ያልተፈቀደላቸው አዋቂዎች ወደ ህንጻው ለመግባት ሲሞክሩ ያሉ የውጭ ጉዳዮች ወይም እንደ ተማሪዎች ሲጣሉ ያሉ የውስጥ ጉዳዮች ለመፍታት ሊያግዙ ይችላሉ።በሁሉም ሁኔታዎች ትኩረታቸው ከደህንነት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ነው።የደህንነት እና ጥበቃ ቡድኑ ጥሩ የትምህርት አካባቢን ለማዳበር እና ለደህንነቱ ያልተጠበቀ ወይም ጤነኛ ያልሆነ ስነምግባር እንደ መከላከያ ሆኖ ለመስራት ፍላጎት አለው።የሕግ አስከባሪ አካላት በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ላይ ሊጠሩ ይችላሉ፣ለምሳሌ በግቢው ውስጥ የጦር መሳርያ ሲኖር፣ካልሆነ ግን አብዛኞዎቹ የደህንነት ጉዳዮች ያለህግ አስከባሪ ተሳትፎ በደህንነት እና ጥበቃ እና በትምህርት ቤት አስተዳደር ቡድን ይስተናገዳሉ።በትምህርት ቤት ውስጥ ደህንነትን ለመጠበቅ እርዳታ ከፈለጉ፣የት/ቤትዎን የደህንነት ባለሙያ፣ርእሰ መምህር፣ወይም የደህንነት እና ጥበቃ ቢሮ በስልክ ቁጥር 206-252-0707 ማግኘት ይችላሉ። (የቦርድ ፖሊሲ ቁጥር 4311 እና የበላይ ተቆጣጣሪ አሰራር ቁጥር 4311SP መልከቱ)።

## ተልዕኮ

ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ተደራሽነትን ለማረጋገጥ እና ለእያንዳንዱ ተማሪ የላቀ ትምህርት ለመስጠት የእድል ክፍተቶችን ለማስወገድ በትጋት ይሰራል።

## ራዕይ

እያንዳንዱ የሲያትል የህዝብ ት/ቤት ተማሪ ከፍተኛ ጥራት እና ዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው ትምህርት ያገኛል እና ለኮሌጅ፣ለሥራ፣እና ለማህበረሰብ ዝግጁ ሆኖ ይመረቃል።

### የእኩልነት እና ተገዢነት ፖሊሲ፡

ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ለሁሉም እኩል የትምህርት እድሎች እና እኩል የስራ እድሎች ያቀርባል።በሁሉም ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ፆታ፤ዘር፤እምነት፤ቀለም፤ሃይማኖት፤የዘር ግንድ፤ብሄራዊ አመጣጥ፤ዕድሜ፤የኢኮኖሚ ሁኔታ፤ፆታዊ ዝንባሌ፣ፆታዊ መግለጫ ወይም ማንነትን ጨምሮ፤እርግዝና፤የጋብቻ ሁኔታ፤አካላዊ ገጽታ፤ማንኛውም የስሜት ህዋሳት፣የአዕምሮ ወይም የአካል ጉድለት መኖር፤በክብር የሰናበተ አርበኛ ወይም የውትድርና ሁኔታ፤ወይም የሰለጠነ የውሻ መመሪያ ወይም የአገልግሎት እንስሳ አጠቃቀም መሰረት በማድረግ አድልዎ አይፈፅምም። የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ለቦይ ስካውት እና ለሌሎች የተመደቡ የወጣቶች ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።ለተማሪዎች እና ለሁሉም የማህበረሰብ ኣባላት የሚከተሉት የመ/ቤቱ ሰራተኞች ጥያቄዎችን ሊመልሱና እና የተፈጸመ መድልዎ አቤቱታዎችን ሊቀበሉ የተመደቡ ስለሆነ ከታች ከተገለፁት በደብዳቤ፣በስልክ ወይም በኢሜይል ልታገኙዋቸው ትችላላችሁ:

*Seattle Public Schools, MS 32-149*
*PO Box 34165*
*Seattle, WA 98124-1165*

**ለጾታዊ መድልዎ ስጋቶች፣ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ:**
Title IX Grievance Coordinator
(206) 252-0367
*title.ix@seattleschools.org*

**ለአካል ጉዳተኝነት መድልዎ ጉዳዮች:**

ADA/Section 504 Grievance Coordinator,
(206) 252-0885
*504coordinator@seattleschools.org*

**ለሁሉም ሌሎች የአድልዎ ዓይነቶች:**

Student Civil Rights, (206) 252-0306
*oscr@seattleschools.org*

ከአካል ጉዳተኝነት የተያያዘ ስለሚሰጥ ኣገልግሎት ወይም ስለሚደረግ አድልዎ፥ ጾታዊ በደልን ጨምሮ በሰራተኞች በኩል የሚነሳ ቅሬታ:

Chief of Human Resources,
*Seattle Public Schools, MS 33-157*
*PO Box 34165*
*Seattle, WA 98124-1165*

*206-252-0024 or hreeoc@seattleschools.org*


### የሲያትል ት/ቤቶች የቦርድ አባላት

*Evan Briggs*
*Sarah Clark*
*Brandon K. Hersey*
*Joe Mizrahi*
*Liza Rankin*
*Michelle Sarju*
*Gina Topp*


Amharic

# ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች

## የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች መሰረታዊ ህጎች

2024 - 2025



ዋና ሃላፊ
Dr. Brent Jones

SEATTLE PUBLIC SCHOOLS

## የተማሪ መብቶች

ተማሪዎች የትምህርት ማህበረሰብ ኣባላት እንደመሆናቸው መጠን የሚከተሉት መብቶች ኣሏቸው:

- አካታች፣ደህንነቱ የተጠበቀ እና እንግዳ ተቀባይ የሆነ መማርያ ክፍል እና የትምህርት ቤት እካባቢ፤
- ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎችን ማግኘት፤
- መታየት፣መታወቅ፣እንክብካቤ ማግኘት፣መሰማት እና ዋጋ ማግኘት፤
- በትምህርት ቤትዎ ሰራተኞች እና በስርአተ ትምህርቱ ውስጥ የባህልዎን እይታ እና ውክልና መኖር፤
- በባህላዊ ምላሽ ሰጪ፣ማህበራዊ ስሜታዊ እና ስነምግባራዊ ድጋፍ ከስህተቶች ለመማር እድል ማግኘት፤
- የዘረኝነት ድርጊትን ያለበቀል ለማሳወቅ ግልፅ መንገድ።

በተጨማሪም፣እንደ ዜጋ፣ተማሪዎች መሰረታዊ መብቶች አሏቸው እና ትምህርት ቤቶች እነዚህን መብቶች ያለአግባብ ሊጥሱ አይችሉም፡

- ከህገወጥ መድልዎ ነጻ መሆን
- የመናገር ነጻነት
- የፕሬስ ነጻነት
- በሰላም የመሰብሰብ ነፃነት
- ቅሬታ ለማቅረብ የድጋፍ ፊርማ የማሰባሰብ ነፃነት
- የሃይማኖት ነፃነት
- የሰከተረያን ቁጥጥር ወይም ተጽእኖ ነጻነት
- ያለምክንያት ያለመፈተሽ እና ያለመታሰር ነፃነት
- በዲስትሪክቱ ጥበቃ ሥር ባሉበት ወቅት ትምህርት የመከታተል ነጻነት
- እኩል የትምህርት ዕድል የማግኘት መብት



## የተማሪ ኃላፊነቶች

እንደ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባል፣ለሚከተሉት የግል ሃላፊነት መውሰድ አለባቹ:

- ሲያስፈልግ እርዳታ መጠየቅ፤
- ሌሎችን በአክብሮት መያዝ፤
- ትምህርት መከታተል እና ለትምህርት መዘጋጀት፤
- የዲስትሪክት እና የትምህርት ቤት ህጎችን መከተል፤
- የአለባበስ ኮድ መከተል(ቦርድ ፖሊሲ ቁጥር 3224)፤እና
- ንብረትን ማክበር (ቦርድ ፖሊሲ ቁጥር.3520።

የእርስዎን ኃላፊነት በተመለከተ ለበለጠ መረጃ፣እባክዎን የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች መሠረታዊ ሕጎች ገጽ 6 ይመልከቱ።

### አንድ ተማሪ ደንብ ከተላለፈ ምን ይሆናል?

የትምህርት ቤት ህግን ከጣሱ፣የሚከተሉትን ለማድረግ መብት አልዎት:

- በዲሲፕሊን ክስተቶች ላይ ወቅታዊ ምርመራዎች፤
- ታሪክዎን መናገር እና በሰነድ ማስቀመጥ፤
- እርስዎ እና ቤተሰብዎ የዲሲፕሊን ውሳኔ/ምላሽ ማብራርያ ማግኘት፤
- ለዲሲፕሊን ክስተት ምክንያታዊ የሆነ የዲሲፕሊን ምላሽ ማግኘት፤
- ከየመጀመሪያ የቃል ማሳወቂያ በኋላ እርስዎ እና ቤተሰብዎ በ 24 ሰዓታት ውስጥ የጽሁፍ ማሳወቂያ ማግኘት፤
- ግንኙነቶችን በቤትዎ ቋንቋ ማግኘት፤
- ይግባኝ ስለማለት መብት መረጃ ማግኘት፤
- በክብር መያዝ እና የታሪክዎን ጎን እንዲናገሩ መፍቀድ፤
- በማንኛውም የዲሲፕሊን ምላሽ ቤተሰብዎ እንዲሳተፍ ማድረግ፤
- ከዘረኝነት ነፃ የሆነ የዲሲፕሊን ምላሽ ከምክንያታዊ ውጤቶች ጋር፣ የማገገሚያ ልምዶችን እና/ወይም ሽምግልናን ጨምሮ፤
- በቤት ቋንቋዎ እንዲያውቁ ማድረግ፤
- ለእገዳ እና መባረር ውሳኔ በአምስት (5) የትምህርት ቀናት ውስጥ እንዲሁም ለየአደጋ ጊዜ መባረር ውሳኔ በሶስት (3) የትምህርት ቀናት ውስጥ ይግባኝ መጠየቅ፤

አንድ የትምህርት ቤት መሪ በአስቸኳይ ተማሪን እንዲያባርር፣በቂ ምክንያት ሊኖረው ይገባል።ሀ) ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ለግዜው እና ለቀጣይ አደጋ የሚያመጣ ከሆነ ወይም(ለ) በትምህርት ሂደት ውስጥ ቁሳዊ እና መጠነ ሰፊ የሆነ ረብሻ ያሳየ ለግዜው እና ለቀጣይ የሚያስፈራ ከሆነ እና ባሳማኝ ሁኔታ ካመነ በአስቸኳይ ተማሪውን እንዲያባርረው ሊያደርግ ይችላል።

ተማሪው ከትምህርት ቤት ከታገደ፣ጠቅላላ ከተባረረ ወይም ለኣደጋ ግዜ ከተባረረ በ24 ውስጥ የተወሰደውን የስነስርኣት እርምጃ የሚገልጽ (ኖቲስ ኦፍ ዲሲፕሊነሪ ኣክሽን (NDA) ደብዳቤ ይደርሳቸዋል።

## የተማሪ የስነምግባር ጥሰቶች

የአካዳሚክ ታማኝነት የጎደለው ድርጊት አስመስሎ ማቅረብ/የሰውን ሀሳብ መውሰድ።
ማቃጠል
ማጥቃት
(አካላዊ) ጥቃት
ኮምፒውተር አላግባብ መጠቀም፣ማደናቀፍ፣እና መተላለፍ
አደገኛ የጦር መሳሪያዎች
አድሎአዊ ትንኮሳ
አድሎአዊ ቋንቋ
አለመታዘዝ
የሚረብሽ ስነምግባር
የአልኮል መጠጦችን ማሰራጨት
ሕጋዊ ያልሆኑ መድኃኒቶች፣ቁጥጥር የሚደረግባቸው መድኃኒቶች ወይም በሃኪም የሚታዘዙ ወይም ከሱፐር ማርኬት ሊገዙ የሚችሉ መድሓኒቶች ማሰራጨት
ማሪዋና ማሰራጨት
የትምባሆ/ኒኮቲን ምርቶችን ማከፋፈል
ንጥቂያ፣ብዝበዛ፣ማስገደድ
ውሸት ማስጠንቀቂያ
የውሸት ሪፖርት
የውሸት ማስፈራሪያዎች
መጣላት
የጦር መሳሪያዎች
ርችቶች፣ፈንጂዎች፣ኬሚካሎች እና ተቀጣጣይ መሳሪያዎች
ቁማር
የግድግዳ ፅሁፍ
ትንኮሳ፣ማስፈራራት ወይም ጉልበተኝነት
የጥላቻ ቡድን ተግባር
ማስጨነቅ
ተገቢ ያልሆነ ቋንቋ
ተገቢ ያልሆነ መንካት
በትምህርት ቤት ባለስልጣናት ላይ ጣልቃ መግባት
የትምህርት ቤት ባለስልጣናትን ማስፈራራት
የብልግና ስነምግባር
የንብረት ጉዳት
የተሳሳተ ውክልና
ሌሎች ልዩ ጥፋቶች
ህገ-ወጥ መድሀኒቶች፣ቁጥጥር የሚደረግባቸው ነገሮች፣በሐኪም የታዘዙ ወይም ያለማዘዣ የሚሸጡ መድሃኒቶችን መያዝ ወይም መጠቀም
የአልኮል መጠጦችን መያዝ ወይም መጠቀም
ማሪዋናን መያዝ ወይም መጠቀም
የትምባሆ/ኒኮቲን ምርቶችን መያዝ ወይም መጠቀም
የተሰረቀ ንብረት መያዝ
ዘረፋ
ደንብ መጣስ
የአልኮል መጠጦችን መሸጥ
ሕገወጥ መድኃኒቶችን፣ቁጥጥር የሚደረግባቸው ነገሮች፣በሐኪም የታዘዙ ወይም ያለማዘዣ የሚሸጡ መድኃኒቶችን መሸጥ
ማሪዋና መሸጥ
የትምባሆ/ኒኮቲን ምርቶች መሸጥ
ፆታዊ ጥቃት
ፆታዊ ትንኮሳ
ስርቆት
የጥቃት ማስፈራሪያዎች
መተላለፍ

### አንድ ተማሪ ፍትሃዊ ያልሆነ አያያዝ እየደረሰበት መሆኑን ቢያስብስ?

የትምህርት ቤቱ መሪ የስነስርዓት እርምጃ ከወሰነ እና ተማሪው ፍትሃዊ ያልሆነ ወይም አግባብ አይደለም ብሎ ካሰበ፣ተማሪው የተጣለበትን እርምጃ አስመልክቶ ይግባኝ የመጠየቅ መብት አለው። የተለያዩ የይግባኝ ሂደቶች በሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች መሰረታዊ ህጎች ላይ ይገኛሉ።ይህ ከተማሪው ትምህርት ቤት፣ ከተማሪው የዲሲፕሊን ቢሮ በ 206-252-0820 ወይም በሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ድረ-ገጽ www.seattleschools.org ማግኘት ይቻላል።



### የ1989 የፌደራል ከኣደንዛዥ ዕጾች ነጻ የሆኑ ትምህርት ቤቶች እና ማሕበረሰቦች ድንጋጌ ለተማሪዎች እና ለወላጆች የሚጠይቀው ማሳሰቢያ

ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሕገወጥ በሆነ መንገድ ኣልከሆል እና ኣደንዛዥ ዕጽ በትምህርት ቤት ግዚ ውስጥ፣በት / ቤት ንብረት ውስጥ፣በት / ቤት ስፖንሰር በተደረገ ትራንስፖርት ወይም በትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ላይ መያዝ፣መጠቀም ወይም ማከፋፈል ይከልክላል።ይህን ሕግ ማክበር የግድ ነው።ይህን ሕግ የሚጥሱ ተማሪዎች የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድባቸው ይችላል።ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የአደንዛዥ ዕፅ እና የአልኮል ትምህርት፣የምክር እና የማገገሚያ ድጋፍ ሊያቀርብ ወይም በማዘጋጀት በኩል ሊረዳ ይችላል።ለበለጠ መረጃ የትምህርት ቤቱን መሪ፣የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሰራተኛ ወይም አማካሪ ያነጋግሩ።